የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ—የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 28
ADDIS ABABA - 5th March 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፬/፲፱፻፺ ዓ.ም
የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ
አዋጅ ...................................................... ገጽ ፯፻፲፬

## CONTENTS

Proclamation No.104/1998
Private Employment Agency
Proclamation ..................................... Page 714

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፬/፲፱፻፺
## ስለግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የወጣ አዋጅ

ሥራና ሠራተኛን በማገናኘት ሥራ ግለሰቦችንና የግል ድርጅቶችን ማሳተፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በተለይ ወደውጭ አገር ለሥራ የሚላኩ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች መብታቸው፣ ደህንነታቸውና ክብራቸው ተጠብቆላቸው የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አዋጅ ቁጥር ፩፻፬/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ" ማለት መንግሥታዊ አካል ያልሆነና ከሚከተሉት አንዱን ወይም ሁለቱን አገልግሎት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሠራተኛው ገንዘብ ሳይቀበል ሥራና ሠራተኛን በማገናኘት ሥራ ላይ የሚሠማራ ሰው ነው፣

## PROCLAMATION NO. 104/1997
## PRIVATE EMPLOYMENT AGENCY PROCLAMATION

WHEREAS, the participation of individuals and private entities in the employment services has become necessary;

WHEREAS, it has particularly become necessary to protect the rights, safety and dignity of Ethiopians employed and sent abroad;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Private Employment Agency Proclamation No. 104/1998."

2. *Definitions*

In this Proclamation, unless the context otherwise requires;

1) "Private Employment Agency" means any person, independent of government bodies, which performs one or two of the following employment services without directly or indirectly receiving payments from the worker;

ሀ) የሥራ ውሉ ተዋዋይ ወገን ባለመሆን በአገር ውስጥ ሥራና ሠራተኛን የማገናኘት አገልግሎት መስጠት፤

ለ) ከሠራተኛው ጋር የሥራ ውል ስምምነት በማድረግ ሠራተኛውን በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር ለሥራ ለሦስተኛው ሰው የማቅረብ አገልግሎት መስጠት፤

፪· "ፈቃድ" ማለት በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚያስችል አግባብ ባለው ባለሥልጣን ለግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ነው፤

፫· "ሠራተኛ" ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፵፪/፲፱፻፹፭ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

፬· "አግባብ ያለው ባለሥልጣን" ማለት ሚኒስቴሩ ወይም በክልል የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎችን የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፤

፭· "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ማለት እንደአግባቡ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ነው፤

፮· "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፯· በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

፫· <u>የአፈጻጸም ወሰን</u>

፩· የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፵፪/፲፱፻፹፭ አንቀጽ ፫(፪)(መ) ቢኖርም ፣ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ፣ አዋጅ ቁጥር ፵፪/፲፱፻፹፭ ለትርፍ በሚካሄድ ሥራ ላይ ላልተመሠረተ የግል አገልግሎት ሥራ ተቀጥሮ በውጭ አገር በሚሰራ ኢትዮጵያዊ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፪· የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፵፪/፲፱፻፹፭ አንቀጽ ፻፸፪ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ አንድን አሠሪ ቀጥታ ቅጥር እንዲያከናውን ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለሥራ ወደውጭ አገር ሊሄድ የሚችለው በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አማካኝነት ብቻ ነው።

፫· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪(፩)(ለ) የተመለከተውን አገልግሎት በሚሰጥ ኤጀንሲ እና በሠራተኛው መካከል ማንኛውም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ እና በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፭ የተጠቀሰው መብት በመጣሱ ምክንያት የሚነሳ ክርክር በአዋጅ ቁጥር ፵፪/፲፱፻፹፭ መሠረት ሊታይ ይችላል።

፬· ይህ አዋጅ ማንኛውም የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ በሌሎች ሕጎች ያሉበትን ግዴታዎች የሚያግድ አይሆንም።

፬· <u>ፈቃድ ስለማስፈለጉ</u>

የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ሆኖ ለመሥራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከሚከተሉት አካላት ፈቃድ ማውጣት ይኖርበታል፤

፩· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሥራና ሠራተኛ አገናኝነቱን አገልግሎት በአንድ ክልል ውስጥ የሚሰጥ ከሆነ ይህንኑ አገልግሎት በሚሰጥበት ክልል ውስጥ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎችን ለማስፈጸም ኃላፊነት ከተሰጠው አካል፤

(a) services of matching offers of and application for local employment without being a party to the employment contract;

(b) services of making a worker available locally or abroad to a third party by concluding a contract of employment with such a worker.

2) "License" means a certificate of competence issued by the competent authority to a private employment agency enabling the agency to engage in employment service activities;

3) "Worker" shall have the meaning as defined in the Labour Proclamation No. 42/1993.

4) "Competent Authority" means the Ministry or a Regional Authority responsible for the implementation of labour laws in the Region;

5) "Minister" or "Ministry" means the Minister or Ministry of Labour and Social Affairs respectively.

6) "Person" means any natural or juridical person.

7) Provisions of this proclamation set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

3. *Scope of Application*

1) Notwithstanding the provisions of Article 3(2)(d) of the Labour Proclamation No. 42/1993, Proclamation No. 42/1993 shall, for the purpose of this proclamation, be applicable to an Ethiopian employed to work abroad for personal services of non-profit making purposes.

2) Without prejudice to Article 172 of the Labour Proclamation No. 42/1993, any Ethiopian may be allowed to go and work abroad only through the private employment agency unless the Minister permits the direct recruitment by an employer.

3) Any labour dispute and other dispute arising under Article 15 of this Proclamation between the agency providing a service specified in Article 3(1)(b) of this Proclamation and the worker may be settled in accordance with Proclamation No. 42/1993.

4) This Proclamation shall not relieve any private employment agency of its obligations imposed by other laws.

4. *Requirement of License*

Any person who wishes to operate a private employment agency shall have to obtain a license from the following authorities;

1) without prejudice to Sub-Article 3 of this Article, from the Regional Authority responsible for the implementation of labour laws, if the employment service is confined within that region;

፪· የሥራና ሠራተኛ አገናኝነቱን አገልግሎት በሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ የሚሰጥ ከሆነ ከሚኒስቴሩ፣

፫· የሥራና ሠራተኛ አገናኝ አገልግሎቱ ኢትዮጵያዊ ሠራተኛን ቀጥሮ ከኢትዮጵያ ውጪ ለሦስተኛ ሰው ለሥራ ለማሰማራት ከሆነ ከሚኒስቴሩ።

፭· ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስላለባቸው ሁኔታዎች

በዚህ አዋጅ መሠረት በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲነት ለመሥራት የሚያመለክት ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፣

፩· በኤጀንሲነት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችለው የንግድ ምዝገባ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ የማቅረብ፣

፪· በዚህ አዋጅ መሠረት ሠራተኛን ለሥራ ወደውጭ አገር በመላክ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ መሠረት የተመለከተውን የዋስትና ግዴታ መሟላቱን የሚያሳይ ማስረጃ የማቅረብ፣

፫· ይህን አዋጅ መሠረት አድርጎ በሚወጣው ደንብ የተወሰነውን የፈቃድ ክፍያ አግባብ ላለው ባለሥልጣን የመክፈል፣

፬· የአደረጃጀት መዋቅሩን የሚያሳይ ቻርትና በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራውን የሚካፈሉ አባሎቹን ዝርዝር የማቅረብ፣

፭· የሥራውን እና የወኪሉን አድራሻ የማሳወቅ፣

፮· ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚጠየቁ መረጃዎችን የማቅረብ።

፮· ፈቃድ ስለመስጠት

በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ለማግኘት የሚያበቁ ሁኔታዎች መሟላታቸው እንደተረጋገጠ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ለአመልካቹ ፈቃድ ይሰጣል።

፯· ለፈቃድ ብቁ ስላለመሆን

በሕገወጥ ሥራና ሠራተኛ ማገናኘት ሥራ ምክንያት በወንጀል የተቀጣ ሰው ለግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲነት ፈቃድ ብቁ አይሆንም።

፰· ፈቃዱ ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ በየዓመቱ የሚታደስ ሆኖ ለ፪ ዓመት ጊዜ የጸና ይሆናል።

፱· ቢሮ መክፈት አስፈላጊ ስለመሆኑ

፩· ማንኛውም የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ለሥራው ማስኬጃ ቢሮ መክፈት ይኖርበታል።

፪· ኢትዮጵያውያንን በሥራ ቅጥር ወደውጭ አገር የሚልክ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ሠራተኛውን በሚልክበት አገር ቅርንጫፍ ቢሮ ወይም ተወካይ ሊኖረው ይገባል።

፲· ፈቃድን በግልጽ ቦታ ስለማስቀመጥ

ማንኛውም የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ፈቃድ በከፈተው ቢሮ ለሌሎች ሰዎች ግልጽ ሆኖ እንዲታይ ማድረግ ይኖርበታል።

፲፩· ቢሮን ስለማዛወር

ማንኛውም የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ቢሮውን ወደሌላ ሥፍራ ከማዛወሩ በፊት በቅድሚያ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማሳወቅ ይኖርበታል።

፲፪· ስለግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲው ግዴታዎች

፩· በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች ከተመለከቱት ግዴታዎች በተጨማሪ ማንኛውም የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ፣

2) from the Ministry if the employment service is to be rendered in two or more regions;

3) from the Ministry if the employment service is to hire and send abroad an Ethiopian worker to a third party.

5. *Conditions Required to obtain a License*

Any person who applies to operate a private employment agency in accordance with this Proclamation shall fulfill the following:

1) present a document that shows he has a business registration for the operation of a private employment service;

2) if he is providing a service of hiring and sending a worker abroad in accordance with this proclamation to present a document that shows he has fulfilled the obligations of guarantee specified in Article 14 of this Proclamation;

3) pay a license fee to the competent authority the amount of which shall be determined by the regulation issued in accordance with this Proclamations;

4) present a chart that shows the organizational structure and the list of members involved in the employment service activities;

5) notify the address of his office and of his representative;

6) present other relevant documents as may be required by the competent authority.

6. *Issuance of License*

The competent authority shall, upon the fulfillment of the required conditions to obtain a license under this Proclamation, issue a license to the applicant.

7. *Disqualification*

A person punished for his engagement in an illegal employment activity shall not qualify for a license to operate a private employment agency.

8. *Validity of License*

A license issued in accordance with this Proclamation shall be valid for two years subject to renewal every year.

9. *Opening of Office*

1) Any private employment agency shall open an office for the operation of its activities.

2) A private employment agency which hires and sends Ethiopians abroad for work shall have a branch office or a representative in the country where he sends the worker.

10. *Displaying of License*

Any private employment agency shall display the license issued to him in accordance with this Proclamation in his office visible to other people.

11. *Transfer of Office*

Any private employment agency shall notify the competent authority prior to transferring his office to another place.

12. *Obligation of a Private Employment Agency*

1) In addition to the obligations specified in this proclamation and other laws, a private employment agency shall have the following obligations:

ሀ) እንደአስፈላጊነቱ የሥራ ፈላጊዎችን አመላመልና ምዝገባ ሥነ ሥርዓት አዘጋጅቶ አግባብ ላለው ባለሥልጣን አቅርቦ የማጸደቅ፣

ለ) ፈቃድ ሲያወጣ ፡ ሲያሳድስና ሲተካ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ የሚፈለግበትን የፈቃድ ክፍያ አግባብ ላለው ባለሥልጣን የመክፈል፣

ሐ) ቢሮውን ለመዝጋት ሲፈልግ በቅድሚያ አግባብ ያለውን ባለሥልጣን የማሳወቅ፣

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪(፩)(ለ) በተመለከተው መሠረት ሥራና ሠራተኛን የማገናኘት ግልጋሎት የሚሰጥ ከሆነ የሥራ ውሉን አግባብ ባለው ባለሥልጣን የማጸደቅ እና የዚሁኑም ትክክለኛ ቅጂ ለዚሁ አካል አቅርቦ የማስመዝገብ ግዴታ አለበት

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ግዴታዎች በተጨማሪ ሠራተኛን ወደውጭ አገር ለሥራ የሚያሰማራ የግል ሥራና ሠራተኛ ኤጀንሲ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፣

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱(፪) መሠረት በውጭ አገር የሚገኘው ቅርንጫፍ ቢሮ የተቋቋመበት ወይም ወኪል የተሰየመበትን ሕጋዊ ሠነድ የማቅረብና የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን ወይም የወኪሉን ሙሉ አድራሻ የማሳወቅ፣

ለ) ሠራተኛው የሥራ ውሉን ከመፈረሙ በፊት ስለሚቀጠርበት ሥራና አገር በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው አስፈላጊ የሆነ መግለጫ የመስጠት፣

ሐ) ሠራተኛው ደመወዙን እንደአግባቡ በከፊል ወይም በሙሉ ወደአገሩ ለመላክ ሲፈልግ በዚያው አገር ሕግ መሠረት አስፈላጊውን ሁኔታዎች የማመቻቸት፣

መ) ሠራተኛው በሄደበት አገር ስለሚገኝበት ሁኔታ በየዓመቱ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በሚኒስትሩ ሲጠየቅ ሪፖርት የማድረግ፣

ሠ) ሥራውን በሚሠራበት ጊዜ የኅብረተሰቡን ሞራልና ባህል የመጠበቅ፣

ረ) የሥራ ውሉን ለማራዘም ወይም ለማሻሻል ሲፈልግ በቅድሚያ ለሚኒስቴሩ አቅርቦ የማጸደቅ እንዲሁም የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ሚኒስቴሩን የማሳወቅ፣

ሰ) የሥራ ውሉ በሚቋረጥበት ወይም ሠራተኛው በሚጠይቅበት በማንኛውም ጊዜ ሲሠራ የነበረውን የሥራ ዓይነት ፡ የአገልግሎት ዘመንና ሲከፈለው የነበረውን ደመወዝ የሚያሳይ የምስክር ወረቀት በነጻ እንዲሰጠው የማድረግ፣

ሸ) ወደውጭ አገር ለሥራ የላካቸውን ሠራተኞች ስም፣ ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ሙያ፣ የተቀጠሩበትን የሥራ ዓይነት፣ ደረጃ ፡ የደመወዝ መጠን ውሉ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜና ሌሎች በሚኒስቴሩ የሚጠየቁ መረጃዎችን በመዝገብ የመያዝና ሚኒስቴሩ በጠየቀ ጊዜ የማሳወቅ፣

ቀ) ወደውጭ ለሥራ የላካቸውን ሠራተኞች በሚሰሩበት አገር አቅራቢያ ላለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ አሳውቆ የማስመዝገብ።

፲፫. *ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ*

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰(፪) እና (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚከተሉት ሁኔታዎች ፈቃድን ሊያግድ ወይም ሊሠርዝ ይችላል፣

(a) to prepare and submit for approval to the competent authority a procedure regarding the recruitment and registration of job-seekers;

(b) to pay the required fee for issuance, renewal and replacement of the license determined by the regulations issued in accordance with this Proclamation:

(c) notify the competent authority prior to closing his office;

(d) to submit the contract of employment to the competent authority for approval and registration of a copy thereof if the agency provides the service specified in Article 2(1)(b) of this Proclamation.

2) In addition to the obligations provided for in sub-Article (1) of this Article, a private employment agency which sends a worker for work abroad shall have the following obligations:

(a) to submit a legal document establishing a branch office or appointing a representative abroad in accordance with Article 9(2) of this Proclamation and notify the address of same;

(b) provide the necessary orientation to the worker with regard to the work and the country of his employment before the contract of employment is signed;

(c) where the worker wishes a full or partial remittance of his wage to his country, to facilitate same in accordance with the laws of the country of employment;

(d) to submit a report to the Ministry annually or as may be required regarding the situation of the worker in the country of employment;

(e) to respect the moral and culture of the society while performing the activity;

(f) to submit for approval to the Ministry prior to extending or modifying the contract of employment and notify the Ministry upon termination of the contract;

(g) upon termination of the contract of employment or whenever the worker so requests, to provide the worker, free of charge, with a certificate stating the type of work he performed, the length of service and the wage he was earning;

(h) to keep a register containing the name, age, educational level, qualification, type of work, position, the amount of wage, duration of the validity of the contract and other particulars which may be required by the Ministry and notify same to the Ministry as may be required;

(i) notify to the Ethiopian Embassy nearest to the country of employment of the workers sent abroad and cause their registration by same Embassy.

13. *Suspension or Cancellation of License*

Without prejudice to Article 18(2) and (3) of this Proclamation, the competent authority may suspend or cancel a license on the following grounds:

፩· ፈቃዱ በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመሥርቶ ለግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲው የተሰጠ ሆኖ ሲገኝ፣

፪· የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲው ወይም ወኪሉ ከሠራተኛ በዓይነትም ሆነ በገንዘብ ክፍያ ተቀብሎ ሲገኝ፣ ወይም

፫· የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲው ሌሎች የአዋጁን ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም ሌሎች ሕጎችን ተላልፎ ሲገኝ፣

፲፬· ስለዋስትና ገንዘብ አስፈላጊነት

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት ሠራተኛን ወደ ውጭ አገር ለሥራ የሚልክ ማንኛውም የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ለሠራተኛው መብት ዋስትና ማስከበሪያ የሚውል ከዚህ በታች የተመለከተውን የገንዘብ መጠን በጥሬ ወይም ከታወቀ የገንዘብ ድርጅት የተረጋገጠና የማይሻር ተመጣጣኝ የዋስትና ወረቀት ማስቀመጥ ይኖርበታል።

ሀ) እስከ አምስት መቶ ለሚደርሱ ሠራተኞች ፴ ሺ የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር፣

ለ) ከአምስት መቶ አንድ እስከ አንድ ሺህ ለሚደርሱ ሠራተኞች ፵ ሺ የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር፣

ሐ) ከአንድ ሺህ አንድ በላይ ሠራተኞች ፶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተቀማጭ የሆነው የዋስትና ገንዘብ መጠን ለሠራተኛው መብት ዋስትና ማስከበሪያ ከዋለ ወይም ተቀናሽ ከሆነ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲው የዋስትናውን ገንዘብ በአሥር ቀን ጊዜ ውስጥ ማሟላት ይኖርበታል።

፫· ከሠራተኛው መብትና ጥቅም ጋር የተያያዘ ጥያቄ ሥልጣን በተሰጠው አካል በመታየት ላይ ካልሆነ በስተቀር ሚኒስቴሩ ዋስትናውን የሚለቀው በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲው አማካኝነት ለሥራ የወጡ ሠራተኞች የሥራ ውላቸው ተቋርጦ ሕጋዊ መብታቸው መከበሩ በተረጋገጠ በ፫ ወር ይሆናል።

፲፭· የሠራተኛውን መብት ስለመጠበቅ

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት ሠራተኛን ወደውጭ አገር ለሥራ በሚልክ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲና በሠራተኛው መካከል የሚደረግ የሥራ ውል ቢያንስ በኢትዮጵያ ሕግ የተመለከቱትን መሠረታዊ የሥራ ሁኔታዎች ለሠራተኛው የሚያስጠብቅ ሆኖ በማናቸውም ሁኔታ ለኢትዮጵያዊው ሠራተኛ በተመሳሳይ የሥራ ዓይነትና ደረጃ ላይ ከሚገኙ አገልግሎቱ ከሚሰጥበት ሀገር ሠራተኞች ያነሰ መብት ወይም ጥቅም የሚሰጥ አይሆንም።

፪· የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት መብትና ጥቅሞች በተጨማሪ የሠራተኛው መብት፣ ደህንነትና ክብር መጠበቁን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

፲፮· ስለቁጥጥር

፩· አግባብ ያለው ባለሥልጣን በማናቸውም የሥራ ሰዓት በቅድሚያ ሳያሳውቅ በማንኛውም የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ቢሮ ለመግባት ፣ አግባብነት ያላቸው ሠነዶችን ለመመርመር ወይም ጥያቄ ለማቅረብ ይችላል።

1) where it is found that the license has been issued to the private employment agency based on deceitful document;

2) where it is found that the private employment agency or his representative has received payment in cash or in kind from the worker; or

3) where it is found that the private employment agency has violated other provisions of this Proclamation or regulations and directives issued in accordance with this Proclamation as well as other laws.

14. *Requirement of Guarantee*

1) Any private employment agency which sends a worker abroad for work in accordance with this Proclamation shall, for the purpose of protecting the rights of the worker, deposits the following amount of money in cash or its equivalent in a confirmed and irrevocable bond from a recognized financial institutions;

(a) for up to five hundred workers 30,000 US Dollar or its equivalent in Ethiopian Birr;

(b) for five hundred and one to one thousand workers 40,000 US Dollar or its equivalent in Ethiopian Birr;

(c) for above one thousand and one workers 50,000 US Dollar or its equivalent in Ethiopian Birr.

2) Where the guarantee fund deposited in accordance with sub-Article (1) of this Article is used up or reduced for the protection and enforcement of the rights of the worker, the private employment agency shall replenish the fund within ten days.

3) The Ministry may release the guarantee fund within 3 months upon the termination of the employment contract and the fulfillment of the legal rights of the worker sent abroad by the private employment agency, unless a claim connected with the worker's rights and benefits is pending before an authorized body empowered to adjudicate such claim.

15. *Protection of the Worker's Right*

1) A contract of employment concluded between the private employment agency which sends workers abroad and a worker shall fulfill the minimum working conditions laid down in the laws of Ethiopia and shall in no circumstance be less favorable to an Ethiopian than the rights and benefits of those who work in a similar type and level of work in the country of employment.

2) The Private employment agency shall, in addition to the rights and benefits provided for in sub-Article (1) of this Article, be responsible to ensure the rights, safety and dignity of the worker.

16. *Inspection*

1) The competent authority shall have the power to enter the office of any private employment agency during any working hour without prior notice, to examine or inquire relevant documents.

፪. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪(፩) (ለ) የተመለከተውን አገልግሎት የሚሰጥ ኤጀንሲ ጊዜው ከማለቁ በፊት የተሰጠውን ፈቃድ ሲመልስ ለሥራ ያሰማራው ሠራተኛ መብቱ እንዳይጓደል አግባብ ያለው ባለሥልጣን ቁጥጥርና ክትትል የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

፲፯. ስለተጠያቂነት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪(፩) (ለ) የተመለከተውን አገልግሎት ለመስጠት ከሠራተኛው ጋር የተደረገ የሥራ ውል ቢጣስ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲውና ሦስተኛው ሰው ለሠራተኛው መብት በጋራ እና በተናጠል ተጠያቂ ወይም ኃላፊ ይሆናሉ።

፲፰. ቅጣት

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው፡

፩. በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ሳያወጣ፡

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራና ሠራተኛን ያገናኘ እንደሆነ ከሦስት ዓመት ባላነሰ ከአምስት ዓመት ባልበለጠ እሥራትና ብር ፲ ሺ (አሥር ሺህ ብር) መቀጫ ይቀጣል።

ለ) ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለሥራ ወደ ውጭ አገር የላከ እንደሆነ ከአምስት ዓመት ባላነሰ ከአሥር ዓመት ባልበለጠ እስራትና ብር ፳፭ ሺ (ሃያ አምስት ሺህ ብር) መቀጫ ይቀጣል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ውጭ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣውን ደንብ ወይም መመሪያ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ፡ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፫ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እስራት ወይም እስከ ብር ፲ ሺ (አሥር ሺህ ብር) መቀጫ ይቀጣል።

፫. ወደውጭ አገር ለሥራ የተላከው ኢትዮጵያዊ ሰብአዊ መብት ፡ አካላዊ ደህንነቱ ላይ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ) የተመለከተው ቅጣት ከ፭ እስከ ፳ ዓመት ጽኑ እስራትና እስከ ብር ፶ ሺ (ሃምሣ ሺህ ብር) መቀጮ ሊደርስ ይችላል።

፲፱. ስለፈቃድ ክፍያ

በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰጥ ፈቃድ የሚጠየቅ ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

፳. ማሻሻያ

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፵፪/፲፱፻፹፭ አንቀጽ ፻፸፮ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፻፸፮ ተተክቷል፡

"፻፸፮. ክልከላ

ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ከሠራተኛ ገንዘብ በማስከፈል ሥራና ሠራተኛን የማገናኘት ተግባር ሊያከናውን አይችልም።"

፳፩. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ሚኒስትሩ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊውን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፳፪. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

2) The competent authority shall be responsible to supervise and control that the rights of the worker, employed by the agency which provides a service mentioned in Article 2(1)(b) of this Proclamation, are not infringed where the license is returned before the date of its expiry.

17. *Responsibility*

The private employment agency and the third party shall jointly and severally be responsible or liable for violation of the contract of employment concluded with the worker to provide the service mentioned in Article 2(1)(b) of this Proclamation.

18. *Penalty*

Unless the provisions of the Penal Code provides more severe penalties, any person:

1) without having obtained a license in accordance with this Proclamation;

   (a) who performs employment services in Ethiopia, is punishable with imprisonment for a term of not less than three years and not exceeding five years and a fine Birr 10,000 (ten thousand Birr).

   (b) who sends an Ethiopian national abroad for work, is punishable with imprisonment for term of not less than five years and not exceeding ten years and a fine Birr 25,000 (twenty five thousand Birr).

2) Who violates this Proclamation and regulations and directives issued in accordance with this Proclamation, apart from what are specified in Sub-Article (1) of this Article and without prejudice to Article 13 of this Proclamation, is punishable with imprisonment upto two years or a fine upto Birr 10,000 (ten thousand Birr).

3) Where the human rights, and physical integrity of an Ethiopian sent abroad for work have been injured, the punishment mentioned in sub-Article (1)(b) of this Article may be increased from 5 to 20 years rigorous imprisonment and a fine upto Birr 50,000 (fifty thousand Birr).

19. *License Fees*

The amount of fees required for a license issued in accordance with this Proclamation shall be determined by the regulations of the Council of Ministers.

20. *Amendment*

Article 176 of the Labour proclamation No. 42/1993 is hereby deleted and replaced by the following new Article 176:

''176. Prohibition

No persons or entity shall perform employment services for consideration from a worker.''

21. *Power to Issue Directives*

The Minister may issue directives necessary for effective implementation of this Proclamation.

22. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 5th day of March, 1998.

Done at Addis Ababa, this 5th day of March, 1998.

NEGASO GIDADA(DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE